ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መ ጀመር

# የመንገድ ደህንነት
# በቤት ውስጥ ትምህርት

ልጆችን በመንገዶቻችን ላይ በደህንነት እንዲሄዱ
የሚረዱ የመማሪያ ልምዶች

Amharic








EARLY LEARNING ASSOCIATION AUSTRALIA

Starting Out Safely

Starting Out Safely

# የመንገድ ምልክቶችን መስራት እና መጠቀም

ልጆች መንገዶችን ሲጠቀሙ ሁሉንም በደህንነት መጓዝ እንዲችሉ የሚረዱ የመንገድ ህጎች/የመንገድ ምልክቶችን መስራት እና መጠቀም።

18ወር – 8ዓመት

*ይህ ልምድ የተሻለ የሚሰራው፦*

**ከ 18 ወር – 8 ዓመት ላሉ ልጆች።**

ትንንሽ ልጆች እርዳታ ይፈልጋሉ፣ ትልልቅ ልጆችን ግን አብዛኛውን ነገር በራሳቸው መስራት ይችላሉ።

## የሚያስፈልጋቹ ነገር

ካርቶን (የቆዩ የምግብ ካርቶኖች ለትንንሽ ምልክቶች ያመቻሉ፤ ትልልቅ ካርቶኖች ደግሞ ለትልልቅ ምልክቶች)፤

ቀለሞች፤

ባለ ቀለም ማርከሮች እና/ወይም ባለቀለም ወረቀት፤

አስፈላጊ ከሆነ የመንገድ ላይ ምልክቶችን የምንሰቅልበት ማስመሪያ ወይም ሌሎች እንጨቶች።







## አሰራር

የራሳችሁን የመንገድ ላይ ምልክቶችን ስሩ – በቤት ውስጥ በመጫወቻ መኪኖች ትንንሽ ምልክቶችን ወይም መጫወቻ ሜዳ ላይ በብስክሌት እና ስኩተር ትልልቅ ምልክቶችን።

ስለ ምልክቶቹ ለማወቅ ቅርጾችን ይሳሉ እና ይህን አገናኝ በመጠቀም ያሳሚሩ። በመንደሮቻችሁ የምታዩትን ምልክቶች መስራት ትችላላችሁ። የምልክቶቹን ምንነት ወይም ትርጉም ከልጆቻችሁ ጋር ተወያዩበት።

ትንንሽ ምልክቶችን በመጫወቻ ባቡር ሃዲድ ወይም የመጫወቻ የመኪና መንገድ ላይ መጠቀም ይቻላል። ከልጆቻችሁ ጋር ስትጫወቱ ስለ መንገድ ምልክቶች እያወራቹ ህጎችን መጠበቅ ትችላላችሁ። *"አ ተመልከቱ፣ ይህ የቁሙ ምልክት ነው። እዚህጋ መቆም አለብኝ።"*

ትልልቅ ምልክቶችን ውጭ ላይ በመስቀል በአትክልት ስፍራ ብስክሌት ወይም ስኩተር ሲነዱ፣ ሲራመዱ፣ ሲሮጡ በንቃት እንዲጫወቱ ማበረታታት ይቻላል።



# የመንገድ ምልክቶችን መስራት እና መጠቀም

Starting Out Safely

### መረጃ ለወላጆች

https://childroadsafety.org.au/parents/parent-resource/

### ልጃችሁ ምን እየተማረ ነው

የመንገድ ህጎች እና ምልክቶች ምን ማድረግ እንዳለብን እንድናስታውስ ይረዱናል።

'መቆም፣ መሄድ፣ በዝግታ መሄድ' እነኚህ ቋንቋዎች የመንገድ ህጎችን እንዲጠብቁ ያግዟቸዋል – ደህንነታቸውን በመጠበቅ።

### ማስታወስ ያለብን ነገሮች

በተለመዱ ምልክቶች ጀምሩ – በመንገድ ላይ ስትሄዱ የተወሰኑትን መርጣቹ መስራት ትችላላችሁ። ልጅዎ እነሱን ሲያውቅ ቀስ በቀስ ተጨማሪ ምልክቶችን ያክሉ።

### ልጃችሁን የምትጠይቁት ጥያቄ እና የምትወያዩባቸው ነገሮች

በመንገድ ስትመላለሱ – "ምን አይነት የመንገድ ምልክቶችን ማየት ይችላሉ?" "እነዚህ ምልክቶች ምን የሚሉ ይመስላችኋል?"

ምልክቶቹ ምን እንደሚያሳዩ አብራሩ – "ምልክቱ በዚህ ጋር መሄድ እንደምንችል ያሳያል፤ ነገርግን ብስክሌት የሚነዱም ሰዎች ስለሚኖሩ ግራችንን ይዘን መራመድ አለብን።"

### እነኚህን ልምምዶችን ማስፋፊያ መንገዶች

የካርቶን መኪና እና የመንገድ ምልክቶችን ተጠቀሙ – እንዴት ማድረግ እንደሚቻል አገናኝ ይመልከቱ።

የመንገድ ደህንነት ሙዚቃን ተጠቅማችሁ ቁም እና ሂድ የሚለውን ጨዋታ ይጫወቱ። ሙዚቃውን ስትጀምሩ እና ስታቆሙ ቁም እና ሂድ የሚሉትን ምልክቶች እያሳያችሁ ልጆቹ መቆምና መሄድን እንዲለማመዱ አግዟቸው።

### ከልጆች ጋር የሚዘመሩ መዝሙሮች

https://childroadsafety.org.au/parents/road-safety-songs/




ጠይቁ...

"ምን ዓይነት የመንገድ ምልክቶችን ታያላችሁ?"

"ምልክቶቹ ምን የሚሉ ይመስላችኋል?"



Starting Out Safely

# ለአሻንጉሊቶች የደህንነት ኮፍያ መስራት

ለአሻንጉሊቶች የደህንነት ኮፍያ መስራት ልጆች በብስክሌት ወይም ጎማ ባለው መጫወቻ ሲጫወቱ የደህንነት ኮፍያ ማድረግ እንዳለባቸው ያስተምራቸዋል።

18ወር – 8ዓመት

*ይህ ልምድ የተሻለ የሚሰራው፡-*

**ከ 18 ወር – 8 ዓመት ላሉ ልጆች።**

ትንንሽ ልጆች እርዳታ ይፈልጋሉ፣ ትልልቅ ልጆችንግን አብዛኛውን ነገር በራሳቸው መስራት ይችላሉ።

## የሚያስፈልጋቹ ነገር

ባዶ የማርማራታ ዕቃ፣ ባዶ የእርጎ ዕቃ ወይም ክብ ዕቃ፤

ሪባን, የቧንቧ ማጽጃዎች ወይም ላስቲክ፤

ስቲከር ወይም ሌሎች ማሳመሪያዎች (አማራጭ)።

## አሰራር

የልጆቻችሁን የአሻንጉሊት ጭንቅላት (ቴዲ ቤር፣ ለስላሳ አሻንጉሊት ወይም አሻንጉሊት) የሚመጥን ከድጋሚ ጥቅም ላይ ከሚውለው ስብስብዎ ያግኙ።

አንዳንድ ሪባን፣ ላስቲክ ወይም የቧንቧ ማጽጃዎችን በመጠን ይቁረጡ።

የተወሰኑ ቀዳዶችን በጎን በኩል መቅደድ ላስቲኮቹን አስገብቶ ማሰር። እንዲሁም እነሱን በላያቸው ላይ መትከል ወይም መሸፈኛ ቴፕ መጠቀም ይችላሉ።

የደህንነት ኮፍያውን ማሳመር።

ልጆቻችሁ ጓደኞቻቸውን በብስክሌት ወይም ጎማ ባለው መጫወቻ ሲያሳፍሩ የደህንነት ኮፍያ እንዲጠቀሙ አበረታቷቸው።






# ለአሻንጉሊቶች የደህንነት ኮፍያ መስራት

Starting Out Safely

## ልጃችሁ ምን እየተማረ ነው

የደህንነት ኮፍያ ማድረግ ከአደጋ ለመጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነው በብስክሌት፣ በስኩተር ወይም በባለጎማ መጫወቻ ስንጫወት።

በቪክቶሪያ የደህንነት ኮፍያ ግዴታ ነው፣ ህጉ ነው።

## ማስታወስ ያለብን ነገሮች

ልጅዎ በተሽከርካሪ መጫወቻ በሚያሽከረክርበት ጊዜ በጓሮው ውስጥ እንኳን ሁል ጊዜም ቢሆን የደህንነት ኮፍያ መልበስ ማለት የማይረሱት ልማድ ይሆናል ማለት ነው። በባለጎማ መጫወቻ ተጫውተው ሲጨርሱ፣ የደህንነት ኮፍያውን ማውለቅ።

አዋቂዎችም የደህንነት ኮፍያ ማድረግ አለባቸው። መልካም ልምምዶችን ሁልጊዜ አርአያ በመሆን አሳዩ።

ከቤታችሁ ጀርባ በቶሎ ተጫውተው ለመመለስም ቢሆን የደህንነት ኮፍያ ያድርጉ።

የፀሀይ ኮፍያ ከደህንነት ኮፍያ ስር ማድረግ ኮፍያው አጥብቆ እንዳይዛቸው ያደርጋል – የፀሀይ ኮፍያውን ያውልቁት (የፀሀይ መከላከያ ክሬም መጠቀም ትችላላችሁ)።

## ልጃችሁን የምትጠይቁት ጥያቄ እና የምትወያዩባቸው ነገሮች

የደህንነት ኮፍያው እንዳይወዛወዝ አጥብቆ ማድረግ ያስፈልጋል የፊቱንም የኃላውንም የጭንቅላታችሁን ክፍል እንዲጠብቅ። ስለዚህ ትክክለኛውን መጠን ያለው ዕቃ መምረጥ።

ጭንቅላታችንን ሁልጊዜ መጠበቅ ይኖርብናል፤ የጨዋታ ጓደኞቻችንም ጭንቅላት እንደዚሁ።

ብለህ ብትጠይቅ "ቴዲ የደህንነት ኮፍያውን አግኝታለ?" ብላችሁ ከጠየቃችሁት ልጃችሁም ሳታስታውሷቸው የእነሱንም ያመጣሉ – ይህ ልጃችሁም ሁልጊዜ የደህንነት ኮፍያውን እንዲለብሱ ያበረታታል።

## እነኚህን ልምምዶችን ማስፋፊያ መንገዶች

ስለ እነኚህም ነገሮች ማሰብ ትችላላችሁ፡-
የራሳችሁን አሻንጉሊት የመኪና መቀመጫ ወይም የብስክሌት መቀመጫ ስሩ ለብስክሌት፣ ለስኩተር።

## የደህንነት ኮፍያ ስለማድረግ መዝሙር

https://childroadsafety.org.au/wp-content/uploads/2020/06/04-Track-4.mp3

## መረጃ ለወላጆች

https://childroadsafety.org.au/parents/helmets/

https://www.vicroads.vic.gov.au/safety-and-road-rules/road-safety-education/helmet-tips-for-parents-and-carers



**ጠይቁ...**

*"ቴዲ የደህንነት ኮፍያውን አግኝቷለች?"*

Starting Out Safely

# ካርታ መስራት

**ካርታ መስራት ልጆች በመንገድ ሲመላለሱ ደህንነታቸውን እንዲጠብቁ እንዲያስቡ እና እንዲያቅዱ ያግዛቸዋል።**

4 – 8 ዓመት

*ይህ ልምድ የተሻለ የሚሰራው፡-*
**4 – 8 ዓመት ለሚሆኑ ልጆች።**

## የሚያስፈልጋቹ ነገር

ወረቀት እና እርሳስ፣ እስክርቢቶ ወይም ከለር

## አሰራር

ካርታውን የምትሰሩትን ቦታ ወስኑ። ልጃችሁ በደምብ ከሚያውቀው ቦታ ጀምሩ፣ ለምሳሌ ከቤታችሁ እስከ ሱቅ ፓርክ ወይም ልጃችሁ የመረጠው ቦታ።

የምትኖሩበትን ቦታ እንዲስል ልጃችሁን ጠይቁት *“ከዛ እዚህ ቦታ እንዴት እንደርሳለን ብላችሁ ጠይቁት ….?”*

ለምሳሌ፣ *“ቤታችንን ልትስል ትችላለህ?” “እና ፓርኩን?” “ከቤታችን ወደ ፓርኩ እንዴት መድረስ እንችላለን?” “ካርታ ልትስልልኝ ትችላለህ?” “ከቤታችን ወደ ፓርኩ ለመሄድ ደህንነቱ የተሻለው አቅጣጫ የትኛው ነው?” “መንገድ ሳንሻገር መድረስ እንችላለን?”*

ልጆቻችሁ ዋና ዋና ቦታዎችን ምልክት የሚሆኑ (ዛፎች፣ ፓርኮች፣ ህንፃዎችን፣ ድልድዮችን) መንገዶችን፣ ሌሎች ቤቶችን እንዲስሉ አበረታቷቸው።

ከዛ፣ ካርታውን ተጠቅማችሁ መዳረሻችሁን ፈልጉ።





# ካርታ መስራት

## መረጃ ለወላጆች

https://childroadsafety.org.au/wp-content/uploads/2020/06/Parent-Resource.pdf

## ልጃችሁ ምን እየተማረ ነው

ልጃችሁ ከቤት ወጥቶ በሚጓዝበት ጊዜ የት እንዳለ እንዲያስብ ማበረታታታችሁ ስለ አካባቢያቸው እንዲያውቅ እና በሚያድጉ ጊዜ ወደፈለጉት መሄድ እንዲችሉ ይረዳዋል።

ወደ አንድ ቦታ ለመድረስ በጣም ደህንነቱ የተጠበቀ መንገድ - የእግረኛ መሻገሪያዎችን ወይም የትራፊክ መብራቶችን በመሳል፣ በተገቢው ጊዜ፣ በካርታው ላይ ወደ አንድ ቦታ ለመድረስ ፈጣኑ መንገድ ሳይሆን በጣም ደህንነቱ የተጠበቀ የሆነውን ማውራት ይችላሉ።

## ማስታወስ ያለብን ነገሮች

ካርታውን ተጠቅማችሁ ያላችሁበትን ቦታ ስትፈልጉ፣ ብዙ ጊዜ ስጡ። ይሄ ፈጣን ጉዞ አይደለም። በምትጓዙበት ጊዜ እጃቸውን ይዛችሁ አቅጣጫ ማየት ስትፈልጉ ቆማችሁ ያላችሁበትን ቦታ ከካርታው ላይ ማይት ይሻላል፤ በአንድ ጊዜ መጓዝም ካርታውንም ለማንበብ ከመሞከር።

ካርታውን በሚስሉበት ጊዜ እና በሚወጡበት ጊዜ፣ ደህንነታቸው የተጠበቁ ቦታዎችን አመላክቷቸው። ለምሳሌ፣ ፖሊስ ጣቢያ፣ የጓደኛ ወይም ዘመድ ቤት፣ አፀደ ህፃናቱን። እርዳታ ቢያስፈልጋቸው ልጆቻችሁ ማንን መጠየቅ እንደሚችሉ አውሯቸው።

## ልጃችሁን የምትጠይቁት ጥያቄ እና የምትወያዩባቸው ነገሮች

በካርታው ላይ ለድህንነት ስጋት ሊሆኑ የሚችሉትን ቦታዎች አውሯቸው ምክንያቱንም ጭምር።

በእነዚህ ቦታዎች ሲደርሱ እንዴት ደህንነታቸውን መጠበቅ እንደሚችሉ አውሯቸው።

## ከልጆች ጋር የሚዘመሩ መዝሙሮች

https://childroadsafety.org.au/parents/road-safety-songs/



**ጠይቁ...**

*“ከቤታችን ወደ ፓርኩ እንዴት መድረስ እንችላለን?”*

*“ካርታ ልትስልልኝ ትችላለህ?”*

# የመንገድ ደህንነት አቅጣጫ ጨዋታ

## የመንገድ ደህንነት አቅጣጫ ጨዋታ በመንገዶች ላይ ደህንነታችን እንዲጠበቅ የሚረዱንን ቃላቶች እና ሀሳቦችን ለመግለጽ የምንጠቀምበት አዝናኝ መንገድ ነው።

3 – 8 ዓመት

*ይህ ልምድ የተሻለ የሚሰራው፡-*
**3 – 8 ዓመት ለሚሆኑ ልጆች።**

### የሚያስፈልጋቹ ነገር

**በሣር ወይም መሬት ላይ የምናስቀምጣቸው ባለቀለም ክብ ወይም አራት መዓዘን ወረቀት** (በሲሚንቶ ላይ በቾክ መሳል የምንችልበት ደህንነት የተጠበቀ ቦታ ካለም ይቻላል ነገር ግን እባክዎ ከመኪና መንገድ የራቀ ይሁን)። 16 ቦታዎች ላይ ምልክት በማድረግ ጀምሩ እና ልጃችሁ የበለጠ መተማመኑ ሲጨምር ቦታዎቹን መጨመር ይችላሉ።

**ካሬ ሣጥን (square box) እንደ እጣ መጣያ መጠቀም እንችላለን።**

**ወረቀት እና ማርከር።**

**ደህንነቱ የተጠበቀ የመጫወቻ ቦታ።**

### አሰራር

**የጨዋታው አላማ ከመጀመሪያው ነጥብ ወደ መጨረሻው ነጥብ መጓዝ ነው።**

**በአንዱ ቦታ መነሻ** በሌለኛው ቦታ **መጨረሻ** የሚል ያስቀምጡ።

**በዳይስ (dice) ላይ እነኚህን 6 መመሪያዎች ይጻፉ –**
ወደፊት፣ ወደኃላ፣ ወደግራ፣ ወደቀኝ፣ ጠብቅ እና ሂድ።

**ባለቀለም ነጥቦቹን በሰንጠረዥ መልክ ሳሏቸው፣** በነጥቦቹ መኃል ያለውን ልዩነት ልጆቻችሁ መራመድ በሚችሉበት መጠን አራርቋቸው።

**ተራ እየተጠባበቃችሁ** ከእናንተ ወይም ከሌላ ልጅ ጋር የዕጣውን ካርቶን (ዳይስ) በመወርወር፣ በካርቶኑ ላይ ያለውን ትዕዛዝ በመከተል ተጫወቱ።

ስትወረውሩ ወደፊት፣ ወደኃላ፣
ወደግራ ወይም ወደቀኝ አንድ እርምጃ ወደ ትክክለኛ መንገድ ተራመዱ፤

ስትወረውሩ ጠብቅ የሚለው ትዕዛዝ ከወጣ፣
ወደየትም አትንቀሳቀሱም፤

ሂድ የሚለው ትዕዛዝ ከሆነ ደግሞ፣
ወደ ፈለጋችሁበት አቅጣጫ መራመድ ትችላላችሁ፤

ስትራመዱ የምትደርሱበት ቦታ ላይ ሌላ ሰው ካለ አብራችሁ
መሆን ትችላላችሁ።







# የመንገድ ደህንነት አቅጣጫ ጨዋታ

Starting Out Safely

## ልጃችሁ ምን እየተማረ ነው

አቅጣጫ የመንገድ ደህንነት ቋንቋዎች ዋና አካል ናቸው – ግራ እና ቀኝ፣ ጠብቅ እና ሂድ የሚሉት ቃላት ስለ መኪኖች እና የሰዎች እንቅስቃሴን ስንመለከት የምንጠቀማቸው ናቸው። ይሄ ጨዋታ ልጆች ደህንነትን እንዲለማመዱ ያግዛል።

## ማስታወስ ያለብን ነገሮች

**የመኪና መንገድ ለመጫወቻ እጅግ አደገኛ ቦታ ነው** – ይህንን ጨዋታ ደህንነቱ በተጠበቀበት ቦታ ለምሳሌ ጓሮ፣ አጥር ባለበት ወይም በረንዳ ላይ መጫወት።

## ከልጆች ጋር የሚዘመሩ መዝሙሮች

https://childroadsafety.org.au/parents/road-safety-songs/

## መረጃ ለወላጆች

https://childroadsafety.org.au/parents/parent-resource/

### እንዴት እንደሚጫወቱ...

*በዳይስ (dice) ላይ እነኚህን 6 መመሪያዎች ይጻፉ – ወደፊት፣ ወደኃላ፣ ወደግራ፣ ወደቀኝ፣ ጠብቅ እና ሂድ።*

*የጨዋታው አላማ ከመጀመሪያው ነጥብ ወደ መጨረሻው ነጥብ መጓዝ ነው።*



Starting Out Safely

# የመንገድ ደህንነት የሐብት አሰሳ

የመንገድ ደህንነት የሐብት አሰሳ ጨዋታ ልጆች በአካባቢያቸው ያሉ የመንገድ ደህንነት መሣሪያዎችን፣ የመንገድ ደህንነትን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው እና የመንገድ ደህንነት ቃላት የሚማሩበት አዝናኝ መንገድ ነው።

3 – 8 ዓመት

*ይህ ልምድ የተሻለ የሚሰራው፦*

**3 – 8 ዓመት ለሚሆኑ ልጆች።**

ትንንሽ ልጆች እርዳታ ይፈልጋሉ፣ ትልልቅ ልጆችን ግን አብዛኛውን ነገር በራሳቸው መስራት ይችላሉ።

## የሚያስፈልጋቹ ነገር

የመንገድ ደህንነት ሐብት አሰሳ ዝርዝር።

ትልልቅ ልጆች የሐብት አሰሳውን ከልጆቻችሁ ጋር ለመጫወት።

## አሰራር

በዝርዝሩ ላይ ያሉትን ነገሮች ከልጃችሁ ጋር የሐብት አሰሳውን ከመጫወታችው በፊት አውሯቸው። ምን ሌሎች ነገሮች ሊያገኙ ይችላሉ– አንዳንድ የራስዎን እቃዎች ወደ ዝርዝሩ ያክሉ።

ልጆችሁ እንኚህ ዓይነት ነገሮች በአቅራቢያ መሆናቸውን ያውቃሉ?

ልጆቻችሁ የሚፈለጉትን ነገር እንዲያስታውሱ ጨዋታውን ከመጀመራችሁ በፊት ዕቃዎቹን ሳሉላቸው።

በአካባቢያቹ እየተራመዳቹ በሐብት አሰሳ ዝርዝሩ ላይ ያሉትን ዕቃዎች ተመልከቱ – ከዝርዝሩ ላይ ምልክት እያደረጋቹ ሂዱ።

እነዚህ ነገሮች በመንገድ ላይ ደህንነትን ለመጠበቅ እንዴት እንደሚረዱን ተነጋገሩ። ለምሳሌ፣ የእግር ዳናው ከመኪናዎች ቀርበን እንዳንጓዝ፤ የመንገዱ ጠርዝ ማገጃው ከመሻገራችን በፊት የመኪናዎችን እንቅስቃሴ እንድንመለከት፤ የፍጥነት ምልክቱ መኪኖች በምን ያህል ፍጥነት እንደሚሄዱ ያሳውቁናል።





# የመንገድ ደህንነት የሐብት አሰሳ

Starting Out Safely

## ልጃችሁ ምን እየተማረ ነው

በአካባቢያቸው ያሉ የመንገድ ላይ ደህንነት መሳሪያዎችን እንዴት መለየት እንደሚችሉ መንገዱን፣ እንዴት ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መጠቀም እንደሚችሉ፣ የመንገድ ላይ ደህንነት የቃላት አጠቃቀም።

## ማስታወስ ያለብን ነገሮች

ደኅንነት ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ።

ይህን ጨዋታ ሲጫወቱ፣ ወይም ሌላ ማንኛውም እንቅስቃሴ፣ በአካባብያችን ስንንቀሳቀስ ደህንነታችንን መጠበቅ ሁላችንም ልናደርገው የሚገባን ነገር ነው።

እንዲህ ልትል ትችላለህ፣ *"እስቲ እዚህ በእግረኛ መንገዱ ላይ እናቆምና የፍጥነት ምልክቱን እንፈልግ ይህም ትኩረታችንን በማየት ላይ እንድናደርግ እና ካገኘን በኋላ መሄዳችንን እንቀጥል።"*

## ልጃችሁን የምትጠይቁት ጥያቄ እና የምትወያዩባቸው ነገሮች

*"ይሄ ለምን ያስፈልገናል?"*

*"ሁሉንም ደህንነታቸው እንዲጠበቅ እንዴት ይረዳናል?"*

*"እነዚህ ሁሉ የትራፊክ ምልክቶች እና መሳሪያዎች እዚህ ባይኖሩ ምን የሚሆን ይመስላችኃል?"*

**መረጃ ለወላጆች**

https://childroadsafety.org.au/pedestrians/children-as-pedestrians/

**ጠይቁ...**

*"ይሄ ለምን ያስፈልገናል?"*

*"ሁሉንም ደህንነታቸው እንዲጠበቅ እንዴት ይረዳናል?"*



# የመንገድ ደህንነት የሐብት አሰሳ

| የመንገድ ደህንነት ዕቃ | የሳላችሁት የዕቃው ምስል | ✓ ✗ |
| --- | --- | --- |
| ቁም ምልክት | | |
| የእግር ዳና | | |
| የእግረኛ መሻገሪያ | | |
| የፍጥነት ምልክት | | |

# የመንገድ ደህንነት የሐብት አሰሳ

| የመንገድ ደህንነት ዕቃ | የሳላችሁት የዕቃው ምስል | ✓ ✕ |
| --- | --- | --- |
| የመኪና መንገድ | | |
| የመንገድ ጠርዝ | | |
| የትራፊክ መብራት | | |
| ደረጃ ማቋረጫ | | |

# የመንገድ ደህንነት የሐብት አሰሳ

| የመንገድ ደህንነት ዕቃ | የሳላችሁት የዕቃው ምስል | ✓ ✕ |
|---|---|---|
| የብስክሌት/ የእግረኛ የጋራ መንገድ | | |
| የራስዎን ይሳሉ | | |
| | | |
| | | |

Starting Out Safely

# የመንገድ ምልክት የካርድ ጨዋታዎች

የመንገድ ምልክት ካርድ ጨዋታን መጫወት ልጆች በመንገዶቻችን ላይ ሁላችንም ደህንነታችንን ለመጠበቅ ስለሚረዱ ምልክቶች እንዲያውቁ ይረዳቸዋል። ልጆች በእነዚህ ምልክቶች የበለጠ ሲጫወቱ ሲወጡ ምን ማለት እንደሆኑ የበለጠ ያውቃሉ።

3 – 8 ዓመት

*ይህ ልምድ የተሻለ የሚሰራው፦*
**3 – 8 ዓመት ለሚሆኑ ልጆች።**

## የሚያስፈልጋቹ ነገር

የቀለም አታሚ ወይም ጥቁር እና ነጭ ማተሚያ
ለ 'እራስዎ ቀለም' ስሪት

ካርዶቹን የምንደግፍበት ካርቶን
(የእህል ወይም የብስኩት ሳጥን ተስማሚ ነው)

ማጣበቅያ

የራስዎን ምልክቶች ቀለም የሚቀቡ ከሆነ ቀለም ያላቸው ምልክቶች

## አሰራር

የካርድዎን አብነት ያትሙ እና አስፈላጊ ከሆነ የቀለም ስሪቱን እንደ መመሪያ በመጠቀም ያቅሏቸው።

ካርዶቹን በቅርፁ ቆርጠን ካርቶኑ ላይ ይለጥፉ

የካርድ ጨዋታዎችን ለመጫወት ካርዶቹን ይጠቀሙ – snap, memory, go fish






# የመንገድ ምልክት የካርድ ጨዋታዎች

### ልጃችሁ ምን እየተማረ ነው

ልጆች በመንገድ ላይ ደህንነታቸውን እንዲያውቁ የሚረዱ ቃላት።

የመንገድ ምልክቶችን እንዴት መለየት እና ትርጉማቸውን ማወቅ።

### ልጃችሁን ልትጠይቋቸው የሚገቡ ጥያቄዎች እንዲሁም ስለ ምን ነገር ማውራት እንዳለብን

*"ይህ ምልክት ምን ማለት ነው"?*

*"ይህን ምልክት ብታይ ምን ታደርጋለህ?"*

ልጅዎ ምልክቱን የማወቅ ችግር ካጋጠመው በእንቅስቃሴ ማሳየት ይችላሉ። ለምሳሌ፣ 'go fish' ውስጥ

*"በዝግታ መሄድ እንዳለብን የሚገልጽ ምልክት አለህ?"*

### ይህንን ልምምድ የምናሰፋበት መንገዶች

ከጓሮው ውጭ በብስክሌቶች እና ስኩተሮች ለመጠቀም የራስዎን ትላልቅ የመንገድ ምልክቶች ይስሩ።

**መረጃ ለወላጆች**

https://childroadsafety.org.au/parents/parent-resource/




**ጠይቁ...**

*"ይህ ምልክት ምን ማለት ነው?"*

*"ይህን ምልክት ብታይ ምን ታደርጋለህ?"*


CHILDREN
STOP
CROSSING








ONLY



RAILWAY
CROSSING


STOP








GIVE
WAY



ONLY



40







40




STOP



ONLY





RAILWAY
CROSSING


GIVE
WAY


CHILDREN
STOP
CROSSING


ONLY



Starting Out Safely

# የመቀመጫ ቀበቶ ደህንነት -
# የካርቶን ሳጥን ተሽከርካሪ መስራት

## የካርቶን ሳጥን መኪና መስራት እና መጠቀም ልጆች ስለ የደህንነት ቀበቶ አስፈላጊነት እና በመኪና ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ እንዴት እንደሚጠብቁን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።

18ወር – 4ዓመት

***ይህ ልምድ የተሻለ የሚሰራው፦***

**ከ 18 ወር – 4 ዓመት ላሉ ልጆች።**

ትንንሽ ልጆች እርዳታ ይፈልጋሉ፣ ትልልቅ ልጆችን ግን አብዛኛውን ነገር በራሳቸው መስራት ይችላሉ።

### የሚያስፈልጋቹ ነገር

ልጅዎ ለመግባት በቂ የሆነ የካርቶን ሳጥን – ትልቅ የናፒ ሳጥን ተስማሚ ነው

የካርቶን መኪና ለማስጌጥ የውበት እቃዎች – ያለዎትን ሁሉ መጠቀም ይችላሉ።

እንደ የደህንነት ቀበቶ ለመጠቀም የሪባን ወይም የጨርቅ ርዝማኔዎች (Upcycling tip - አሮጌ ቲሸርት በቆርቆሮ መቁረጥ መጠቀም ይችላሉ)።

እንደ መሪነት የሚያገለግል ክብ ነገር – ለምሳሌ ወረቀት ወይም የፕላስቲክ ሳህን።

### አሰራር

ጎኖቹን ብቻ ትታችሁ፣ ከላይ እና ከታች ካርቶኑን ቁረጡት።

እንደ መቀመጫ ቀበቶ ለመጠቀም የሪባን ወይም የቴፕ ርዝማኔዎችን እንደ ማሰሪያ ይጨምሩ እና መኪናውን በሳጥኑ ውስጥ አንዳንድ ቀዳዳዎችን በመምታት እና ሪባንን በማሰር መኪናውን ወደ ላይ ይያዙ።

ካርቶኑን (box) በእጅስራዎች ማስዋብ።

ለተወዳጅ አሻንጉሊት እንደ የመኪና መቀመጫ ከኋላ ትንሽ ሳጥን ይጨምሩ - ለአሻንጉሊት ትክክለኛውን የደህንነት ቀበቶ አይርሱ።

ይግቡ፣ የመቀመጫ ቀበቶዎን ይሰሩ እና ይሂዱ!

ስለ መቀመጫ ቀበቶ እና የመኪና መቀመጫ ደህንነት ይነጋገሩ።



# የመቀመጫ ቀበቶ ደህንነት - የካርቶን ሳጥን መኪና መስራት

## መረጃ ለወላጆች

https://childroadsafety.org.au/cars/child-car-seats/

## ልጃችሁ ምን እየተማረ ነው

ደህንነትን የሚገልጹ ቃላት እና በመንገድ ላይ ደህንነትን ስለመጠበቅ የልጆችን ትምህርት የሚደግፉ።

እያንዳንዱ ሰው ደህንነቱን ለመጠበቅ በመኪና ውስጥ ተስማሚ የመቀመጫ ቀበቶ ወይም የመኪና መቀመጫ ያስፈልገዋል።

## ማስታወስ ያለብን ነገሮች

የመንገድ ደህንነት ቋንቋን የበለጠ በተጠቀምን ቁጥር ልጆቻችን ይበልጥ እንዲለማመዱ ያግዛቸዋል። ይህ የመንገድ ህጎችን ለመረዳት ቀላል ያደርገዋል እና የመንገድ ደህንነትን አስፈላጊነት በዕድሜ እየገፉ ሲሄዱ ቀላል ያደርገዋል።

## ልጃችሁን የምትጠይቁት ጥያቄ እና የምትወያዩባቸው ነገሮች

*"ሁሉም ሰው በመኪናው ውስጥ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው?"*
*"የደህንነት ቀበቶዎች አድርጋችኋል?"*
*"ለመሄድ ደህንነታችን የተጠበቀ ነው? እሺ፣ እንሂድ"*

እንደ ቁም፣ ሂድ፣ ፍጣን፣ ዝግ በል የሚሉት ሃሳቦች ተወያዩበት።

ለልጆቻችሁ የትራፊክ ምልክቶችን (እንዴት እንደሚሠሩ የእኛን ግብአት (resource) ይመልከቱ) ከፍ አድርጋችሁ በማሳየት እነኚህን ትዕዛዞች ይስጡ – ቆም፣ ሂድ፣ ቅድሚያ ስጥ፣ በዝግታ ሂድ።

## ከልጆች ጋር የሚዘመሩ መዝሙሮች

https://childroadsafety.org.au/parents/road-safety-songs/

## ይህንን ልምምድ የምናሰፋበት መንገዶች

የራሳችሁን የመንገድ ምልክቶችን ይስሩ እና በቤት ውስጥ ወይም በጓሮው ውስጥ ያስቀምጧቸው። ይህንን እንዴት ማድረግ እንዳለብን የእኛን የመንገድ ምልክቶች እንቅስቃሴ ይመልከቱ።




**ጠይቁ...**

*"ሁሉም ሰው በመኪናው ውስጥ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው?"*
*"የደህንነት ቀበቷችሁን አድርጋችኃል?"*

# በፕራም (pram) ከልጆች ጋር በእግር ለመጓዝ - ቁም ተመልከት አድምጥ አስብ

ከልጅዎ ጋር በፕራም ውስጥ ሲሆኑ ከእግር ጉዞ ጋር መሄድ ጥሩ መንገድ ነው እንደ ተሳፋሪ ደህንነትን እንዲያውቁ እና እንዴት ማቆም እንደሚችሉ እንዲያውቁ ለመርዳት እና ሲወጡ እና ሲሄዱ እዲያዳምጡ እዲያስቡ።

ከውልደት – 3ዓመት

*ይህ ልምድ የተሻለ የሚሰራው:-*

**ከውልደት እስከ 3 ዓመት ላሉ ልጆች።**

## የሚያስፈልጋቹ ነገር

ደህንነቱ የተጠበቀ ፕራም ወይም ጋሪ።

ደህንነቱ በተጠበቀ ፕራምስ እና ጋሪ ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ወደዚህ ሊንክ ይሂዱ https://www.productsafety.gov.au/products/babies-kids/kids-equipment/prams-strollers

ጠቃሚ ምክሮችን ለመግዛት እና ደህንነቱ የተጠበቀ አጠቃቀምን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ወደ ይሂዱ https://raisingchildren.net.au/babies/safety/equipment-furniture/pram-stroller-safety

ይህ ደግሞ ልጅዎን በህፃን ተሸካሚ ሲሸከሙ ወይም በእጃችሁ ሲይዙ ሊደረግ ይችላል። ይሁን እንጂ፣ የሕፃናት ተሸካሚዎች ከ 4 ወር በታች ለሆኑ ህጻናት አይመከሩም።

ለበለጠ መረጃ ወደ ይሂዱ https://raisingchildren.net.au/newborns/safety/equipment-furniture/baby-carrier-sling-safety.

## አሰራር

ልጅዎ በፕራም ውስጥ በደህና መያዙን ያረጋግጡ - የትከሻ ማሰሪያዎችን ጨምሮ፣ መታጠቂያው በትክክል በመገጣጠም።

ልጅዎን በፕራም ውስጥ ሲያስሩ ምን እየሰሩ እንደሆነ እና ለምን እንደሆነ ያስረዱ።

ከአጭሩ ወይም በጣም ምቹ መንገድ ይልቅ፣ ሁል ጊዜ በአስተማማኝ መንገድ ይሂዱ።





# በፕራም (pram) ከልጆች ጋር በእግር ለመጓዝ - ቆም ተመልከት አድምጥ አስብ

Starting Out Safely

### ልጃችሁ ምን እየተማረ ነው

በጉዳናዎች ላይ ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ስለመጓዝ ብዙ ንግግር። የመንገድ የተለያዩ ክፍሎች ስም፣ የእግረኛ መንገድ፣ የትራፊክ ማብራት፣ የመንገድ ጠርዝ የሚሉትን ጨምሮ።

በደህንነት መራመድን ቆም ነገር ስታደርጉ – የልጆቻችሁን ደህንነት እየጠበቃችሁ ነው።

ልጆች በዚህ ዕድሜያቸው ማቆም፣ ማየት፣ መስማት እና ማሰብን መማር ያለባቸው ለምን እንደሆነ እንዲገነዘቡ አንጠብቅም፤ ሆኖም ይህን ጽንሰ ሐሳብ በደንብ ካወቁ በኋላ ላይ ይህን ማድረግ እንዳለባቸው ማስታወስ ቀላል ይሆንላቸዋል።

### ማስታወስ ያለብን ነገሮች

ጥሩ አርአያ ይሁኑ - ስለዚህ ልጅዎ እንዴት ማድረግ እንደሚችሉ ያሳዩት፡-

- በእግረኞች ማቋረጫዎች ወይም የትራፊክ ማብራት (ካለ) በኩል ተሻገሩ እና መንገዱን ስትሻገሩ በመኪናዎች መካከል ከማቋረጥ ይቆጠቡ።
- የእለፍ ምልክት የሚያሳየውን የአረንጓዴ መብራት ሳይበራ እንዳትሻገሩ።
- መሻገሪያ ከሌለ ለመሻገር በጣም አስተማማኝ፣ ግልጽ እና ለእይታ አመቺ የሚሆነውን መሻገሩያ ይምረጡ።
- መንገዱን ከማለፍዎ በፊት ሁል ጊዜ ሁለቱንም መንገዶች ይመልከቱ።
- ከመሻገርዎ በፊት በመንገዱ ላይ ያተኩሩ (በፍፁም በስልክ አይጠቀሙ ወይም ከሌላ ትልቅ ሰው ጋር አይነጋገሩ)።
- በመኪና መንገዶች ውስጥ ሁል ጊዜ የሚንቀሳቀሱ መኪናዎችን ይከታተሉ።

### ልጃችሁን የምትጠይቁት ጥያቄ እና የምትወያዮባቸው ነገሮች

ከጨቅላ ህጻን/ልጅ ጋር ለምን በመንገዱ ጠርዝ ላይ እንደሚቆሙ፣ ከመኪና መንገዶች የሚወጡትን መኪኖች እንደሚፈልጉ እና ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን እንዴት እንደሚያውቁ ያነጋግሩ። ለምሳሌ፡-

*"የሚንቀሳቀሱ መኪኖችን እየተመለከትኩ ነው።"*
*"ብስክሌት ሲመጣ ታያለህ?"*
*"በፍጥነት እየነዱች ነው፣ ስለዚህ ቆመን እንጠብቃለን።"*

*"ለመሻገር ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን።"*

*"ወደ የትራፊክ መብራቶች እንጢጋ፣ በዛ በኩል መሻገር የበለጠ አስተማማኝ ነው።"*

*"የመንገዱ ጠርዝ ላይ ስንደርስ፣ ሁልጊዜ ቆሜ የሚመጣ መኪና ካለ አረጋግጣለው።"*

*"ከባድ መኪና እሰማለሁ፣ የት እንዳለ እስክናይ ድረስ እንጠብቅ?"*

### ከልጆች ጋር የሚዘመሩ መዝሙሮች

ስለ መንገድ ደህንነት ለልጆች ዘፈኖችን መዘመር ይችላሉ። ልጆች መዝሙሩን ደጋግመው ሲሰሙት ይለምዱታል – መዝሙሩን ማወቅ ልጆች እያደጉ ሲመጡ ከሃሳብ ጋር እንዲቀራረቡ ይረዳቸዋል። ከዛ ልጆቹ ሲያድጉ ድርጊቱን ደግሞ ይማራሉ።

ይመልከቱ link

**መረጃ ለወላጆች**
https://rednose.org.au/article/prams-and-strollers



**ጠይቁ...**
*"ወደ የትራፊክ መብራቶች እንጢጋ፣ በዛ በኩል መሻገሩ የበለጠ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው።"*

*"ለመሻገር ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን።"*

## ማስታወሻዎች

ተጨማሪ መረጃ > childroadsafety.org.au

ROAD SAFETY EDUCATION VICTORIA

Starting Out Safely

EARLY LEARNING ASSOCIATION AUSTRALIA

VICTORIA State Government